# ስለ እግዚአብሔር ፍቅር


“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)



God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395



ግንቦት 1995 May 2003 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54÷13)


# አዲስ አማኝ ነኝ

## ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ አለብኝ?

ሰው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በልዩ ልዩ ሁኔታና አኳኋን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊመጣ ይችላል። በአማኞች ምስክርነት ልቡ ተነክቶ÷ ወይም በታላቅ ቀውጢ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ደርሶለት ጌታን በመቀበል ሰው ዳግመኛ ልደት ሊያገኝ ይችላል። አንዳንዶቻችን ዳግመኛ ልደት ያገኘነው በቤተ ክርስቲያን በሕዝቡ ፊት ወጥተን ተጸልዮልን ነው። ሌሎቻችን በገዛ ቤታችን ተንበርክከን ራሳችንን በመስጠት ነው የዳንነው። አንተስ? ድነሃል?

መዳንህን የማታውቅ ከሆንህ ግን አንድ መፍትሔ ነው ያለህ። ዛሬውኑ በጌታ በኢየሱስ ዕመን። የንስሐ ፀሎት ከአፍህ አውጥተህ ፀልይ። ከዚያም ይህን ያደረግኸውን ውሳኔ ማለትም ጌታን መቀበልህን ምስክርነት እንዲሆንልህ ለሰው ተናገር፡መስክርም

---

የንስሐ ፀሎት፡-
እግዚአብሔር ሆይ÷ደኅንነቴን ለማረጋገጥ በሚታወቀኝ አኳኋን ልጅህን ኢየሱስን አሁን እቀበላለሁ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ስለኃጢአቴ መሆኑን አምናለሁ። በቀረኝ ዘመኔ ከሐጢአት ርቄ እኖራለሁ። ለክብርህም እኖራለሁ። በመንግሥትህ ተቀበለኝ። ስለ ስምህ። አሜን።

---

ቀደም ሲል ሆነ አሁን ከዚህ በላይ ያለውን ፀሎት በመፀለይ ደኅንነትን የተቀበለ ሰው፡- _ከዳንሁ በኋላ ምን እንደማደርግ አልገባኝም_ ይል ይሆናል። የሚከተሉት በእንዲህ ያለ ሁኔታ ያሉትን ወገኖች ሊረዱ የሚችሉ ጠቃሚ ምክሮች ናቸው።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ወደ መንግሥቱ የጠራን ታላቅ የዘላለም ደስታ ድግስ አዘጋጅቶ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ይህንንም ለማድረግ አሁን ካለንበት ሁኔታ እውጥቶ እጅግ ወደ ተለየ መንፈሳዊ ዕድገትና ለውጥ ያመጣናል። በሕይወታችን በታዘዝን መጠን ወደ አዲስና ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ እያሸጋገረ ያሳድገናል። ከዓመት ወደ ዓመት እግዚአብሔርን ማወቃችን እየጨመረ÷ ዕምነታችን እያደገ÷ ክርስትናችን እየጣፈጠን ይሄዳል። ዳግመኛ ሳይወለዱ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱ ሰዎች ግን ዕድሜአቸውን በሙሉ ይህን መንፈሳዊ ደስታ ሳያዩ ያልተነቃቁ ክርስቲያኖች ሆነው ይኖራሉ። ነገር ግን ማንም ሰው በማንኛውም ጊዜ ጌታን መቀበል ይችላል።

እግዚአብሔርን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እያወቅንና ለእርሱ ያለን ፍቅር እየጨመረ ሲሄድ÷ይህንኑ ፍቅራችንን ለሌሎች የማካፈል ፍላጎታችን ከፍተኛ እየሆነ ይሄዳል። አማኞች ስለክርስቶስ ለሰው መመስከር የምንወድበት ምክንያት ለዚህ ነው። የጠቀመንና የጣፈጠንን ሕይወት የማካፈል ጉዳይ ነው።

# ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር መልካም ወዳጅነት

_ክርስትናን ከሌሎች ኃይማኖቶች የሚለየው አስጨናቂና ድፍንፍን ሳይሆን በነፃነትና እግዚአብሔርን በማወቅ የተሞላ መሆኑ ነው።_ ክርስትና ሰው ራሱን ለማዳን የሚሰቃይበት _ኃይማኖት ሳይሆን_ ማዳን የሚቻለውን÷ለሰውም አለመብቃት የሞተውን ኢየሱስን አምኖ በመዳን _እርሱን የመከተል ሕይወት_ ነው።

## _በዚህ ሕይወት እንዴት እናድጋለን?_

መልካም ያልሆኑ ሃሳቦች÷ስሜቶችና ተግባሮች ቢኖሩብህ ተናዝዘህ ንስሐ ግባ። እግዚአብሔር ያውቃቸዋል፤ ሆኖም ሕይወትህን ከማጽዳቱ በፊት ፍላጎትህን ከአንተ መስማት ይፈልጋል።ከሰዎችም ጋር ሐቀኛ ሁን። ክርስትናን በማስመሰል ከጀመሩ ማቆም በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ ዕውነተኛ ሁን። እግዚአብሔር በሁሉ አቅጣጫ በሕይወትህ እንዲሠራ ፍቀድለትና ሰዎች መንፈሳዊ ዕድገትህን ይዩ።

ጌታ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላህ ለምነው። ከዚያም የመንስ ቅዱስን ድምፅ ሰምቶ መታዘዝን በጥንቃቄ ተለማመድ።

መጽሐፍ ቅዱስን አዘውትረህ በማንበብ ቃሉ በሕይወትህ ውስጥ ሥራውን ሠርቶ እንዲቀድስህና እንዲያበጅህ ጸልይ።

ቀድሞ ትወዳቸውና ታከብራቸው የነበርሃቸውን ነገሮች ለመተው ፈቃደኛ ሁን። የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሚሻልህና ምናልባትም ዋጋ ሊያስከፍልህ እንደሚችል አስተውል።

ስለ ተወሰነ ነገር ጌታ ፈቃዱን ሲገልጽልህ ዋጋህን በዕምነት ተምነህ በቆራጥነት ተከተለው።ከዚያም ጌታ ወደ በለጠ ሁኔታ ሲያሸጋግርህ አስተውል። ሁል ጊዜ በሚታየው ብቻ አትመራ÷ መንፈሳዊ ራዕይ ይኑርህ።

እግዚአብሔር ብልሹ ሕይወትህን አበጃጅቶ እጅግ ታላቅና ብርቱ አገልጋዩ ሊያደርግህ እንደሚፈልግ ዕመን።

ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን አመስግን። በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ስለማይሳካላቸው ትሑት ሁን። ይበልጥ ይከናወንልሃል።

ክፉ ሲያጋጥምህ በእግዚአብሔር በመተማመን በቆራጥነት ጽና። በግልጽ የነገሩን ስም ጠርተህ ፀልይና ጌታ የሚያደርግልህን ድንቅ ተጠባበቅ።

በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፡- በፍቅር÷ደስታ÷ሰላም÷ትዕግሥት÷ቸርነት÷በጎነት÷እምነት÷ታማኝነት÷ ገርነትና ራስን በመግዛት፡ ለማደግ አትስነፍ። እነዚህ ባንተ ሲገለጡ የእግዚአብሔር ሥራ ለሌሎች ይታያልና፤ በሕይወትህ ወንጌልን ለማሳየት አትስነፍ።

ጌታ በፍቅራችን እንድንታወቅ ስላዘዘን ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ ውደድ።

ጌታ የሰዎችን ሕይወት የሚለውጠው ደረጃ በደረጃ ስለ ሆነ÷ለሰዎች ከመሰከርህ በኋላ÷ ቶሎ ውጤት ባታይ አትደነቅ። ተስፋም አትቁረጥባቸው። ይልቁን ጌታ ወደ ደኅንነት እንዲያመጣቸው ያለመሰልቸት ፀልይ።

ስለ ጌታ ለሰው የመንገር ፍርሐት ካለብህ ፍጹም ፍቅሩ ፍርሐትህን እንዲያስወግድልህ ፀልይ እንጂ አትታክት።

ለሰዎች ስለ ጌታ ስትመሰክር ሳታዳምጥ ለመናገር አትቸኩል። ከጌታ እየተማርህ÷ ዕምነትህን ለሌሎች እያካፈልህ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ፍሬያማ ክርስቲያን (ደቀ መዝሙር) ትሆናለህ። እግዚአብሔር ይመስገን።

(ከማመን በኋላ ያለው ጉዞ The Journey Beyond Beliefe ከተሰኘ መጽሐፍ ተወስዶ ከተዘጋጀ መልዕክት ተርጉመን አቀረብን)

---

# ምስክርነት

_ከመጋቢት 1995 (March 03) መልክት የቀጠለ_

በመጋቢት የምስክርነት መልክት ስለ ሸክም አስፈላጊነት በመግለጽ ነበር ያቆምነው። ሸክም ለሚጠፉት ነፍሳት ማዘንና ሁሉም እንዲድን የመፈለግ ጫና ነው።

ጌታ ኢየሱስ ለሕዝቡ ሸክም ነበረው። አንድ ቀን ኢየሩሳሌምን ተመልክቶ እንዲህ አለ፡“ኢየሩሳሌም፡ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር÷ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደ ምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፤ አልወደዳችሁምም።” (ማቴ 23÷37)
ሐዋሪያው ጳውሎስም እንደዚሁ ለሕዝቡ ሸክም ነበረው።“ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ (እስራኤላውያን) ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና” ይላል። (ሮሜ 9÷ 1-3) ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን የመሰለ ሸክም ለሕዝቡ እያለው አገልግሎቱ እንደዚያ መሳካቱ ምን ያስገርማል?
ሌላኛው ታላቅ እግዚአብሔራዊ ሸክም የነበረው ሰው ነኅምያ ነበር። እርሱም በፋርስ ንጉሥ ቤተ መንግሥት በጠጅ አጋፋሪነት ምቹ ኑሮ ነበረው። ምንም እንኳን እንደ ተቀሩት አይሁድ ስደተኛ ቢሆንም÷ የንጉሣዊ ኑሮ ተካፋይነት ዕድል ነበረው።አንድ ቀን ኢየሩሳሌምን ጎብኝተው የተመለሱ ወንድሞቹ ከተማዪቱ በፍርስራሽ መገኘቷን አወሩለት ። ነኅምያም ለእግዚአብሔር የተለየ የቅዱስ ሕዝብ ልዩ ምልክት ሆና እያለች፡- ቅጥሯም የታቦቱ ማደሪያ እንዳልነበረ÷ አሁን ግን ፍርስራሽ መሆኗን አሰበና ፡-

በታላቅ ሐዘን÷ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ካለቀሰ በኋላ ግን የፈረሰውን ቅጥር ለመሥራት በቆራጥነት ተነሣ::

“ካሕን ስላይደለሁ÷ አያገባኝም:: ተነሥቼ ስለ ሐገሬ ብናገር በንጉሡ ዘንድ ያለኝን ዕድል አበላሻለሁ:: ነቢይ ተነሥቶ ሕዝቡን ይቀስቅስ:: እከዚያው ዝም ልበል” ማለት ይችል ነበር:: ነገር ግን ነቢይም ካሕንም ባይሆንም እንኳን ተነሥቶ ለውጥ ማምጣት እንደሚችል አምኖ ተነሣ:: ፀልዮ ከንጉሡም ፈቃድ አግኝቶ ራሱ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ሁኔታውን አጠና:: ከዚያም ዕቅድ አወጣና ሥራ ላይ ማዋል ጀመረ::

አያችሁ? ማሰብ ብቻ÷መፀለይም ብቻ አይበቃም:: ዕቅድ ማውጣትና መነሣት ያስፈልጋል:: ሕዝቡ በፈርዖን ሠራዊትና በቀይ ባሕር መሐል ሆኖ በጨነቀው ጊዜ ጌታ ለሙሴ:- “ለምን ትጮህብኛለህ? እንዲጓዙ ለእስራኤል ልጆች ንገር::” ነበር ያለው:: (ዘጸአት 14÷15)

ለመጸለይ ጊዜ አለው::ለመንቀሳቀስም ጊዜ አለው::ነገር ግን የነገሩ ሁሉ መጀመሪያ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የነፍሳት ፍቅር (ሸክም) ነው::ታዋቂው አሌግዛንደር መክሊን:-“አንድ ክርስቲያን ለነፍሳት ያለውን ፍቅር ንገረኝና ምን ያህል ጠቃሚ ሰው መሆኑን እነግረሃለሁ” ያለው ይታወሳል:: ዕውቁ እንግሊዛዊ ስፐርጀን ደግሞ “ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር የሚያመጡ ለነፍሳት የሚያለቅሱት ናቸው” ብሎ አል:: ስለዚህ ዕምነታችንን ለሌሎች ለማስተላለፍ የነፍሳት ፍቅር ወሳኝ ነው::

# አንድ ሰው እንኳን ወደ ጌታ መርቶ አለማወቅ

አንድም ሰው ወደ ጌታ መርተው የማያውቁ ሰዎች ችግራቸው “ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ አምነህ ትቀበላለህን?” ብለው ማንንም አለመጠየቃቸው ነው:: ሰዎችን ማነጋገር ይጀምሩና በመጨረሻ ላይ ይፈራሉ:: እምቢ ቢሉስ? እያሉ ነው:: ነገር ግን ደፍረን ዕምነታችንን ለሰው መንገር ብንቀጥል ጌታ እንደ ፈቀደ መጠን ሰዎች ይድናሉ:: ከዚያም አንድ ሰው እንኳን በምስክርነታችን ጌታን ሲቀበል የሚፈስስብን ታላቅ የሐሴት መንፈስ የማይረሳና የማይጠገብ ነው::

አልፎ አልፎ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ እንጋብዛለን:: ሆኖም አንዴ እምቢ ሲሉንም ፈጥነን እንተዋቸዋለን:: የኢየሱስን አዳኝነት አምነው በመቀበል እንዲድኑ ሰዎችን መወትወት እንደመጋፋት እንቆጥራለን:: በዕውነቱ ግን ወደ ሲዖል የሚወርድን ሰው ቢገፉት ከዚያ አልፎ የት ሊደርስ ነው? በአጉል አይሁን እንጂ÷ ሰውን ገፍቶ ከዘላለም እሳት ማዳን ቢቻል ምን አለበት?

እስቲ አስቡት፤ ክርስትና ዕውነት ነው? ሲዖል በዕውነት ሰው ለዘላለም የሚሰቃይበት ቦታ ነው? መንግሥተ ሰማይ ለመግባት በኢየሱስ ማመን ግዴታ አይደለም? አዎን በእርግጥ ይህ ሁሉ ዕውነት ነው:: እንግዲያውስ ሰውን ስለመጋፋት የምን ጨነቀው ለምንድን ነው? ለምንስ ቸልተኞች እንሆናለን?

ከብዙ ዓመታት በፊት በእንግሊዝ ሐገር ቻርለስ ፒስ የተባለ ወንጀለኛ ተይዞ ታሰረ:: በተወነጀለበት የሁለት ነፍስ ግድያ÷ በዝርፍያና ሰነድ በመለወጥ በደለኛ ሆኖ ስለ ተገኘ÷ሞት ተፈረደበት:: የሞት ፍርዱ በሚፈጸምበት ዕለት በደለኛው (ጋሎው) ወደሚባለው መስቀያ ሲቀርብ ካሕኑ በአጠገቡ ነበረ:: ካሕኑም የተለመደውን ሥርዓት ያኪያሄድ ነበር:: እርሱም በተማረው መሠረት ኢየሱስ ኃጢአትህን ይቅር ይልሃል÷ መተላለፍህንም ይደመስስልሃል፤በእርሱ የሚያምን ከዘላለም ሞት ይድናል÷እያለ እየደገመ ወደ መሰቀያው ይከተለው ነበረ::

በዚህን ጊዜ ወንጀለኛው በድንገት ወደ ቄሱ ዘወር አለና÷ በቃለ አጋኖ “በዕውነት ይህን የምትለውን ታምናለህ?” ሲል ጠየቀው:: ከዚያም ቀጠለና “እኔ ግን ይህን አንተ የምትለውን ባምን÷ በብርጭቆ ስብርባሪ ላይ በእንግሊዝ ሐገር ዙሪያ በጉልበቴ እዞራለሁ” አለው::

አያችሁ? በዕምነታችን ዕውነተኞች ከሆንን የሚጠፉት ነፍሳት ጉዳይ አጣዳፊነትና አሳሳቢነት ዕረፍት ሊነሣን ይገባል:: <u>*በዚህ አጋጣሚ ብዙ ሰዎችን ከዘላለም ጥፋት ለማዳን እግዚአብሔር ሊጠቀምባችሁ እንደሚፈልግ ላሳስባችሁ አወዳለሁ::*</u>

ምክንያቱም ዛሬም “<u>ማንን እንላክ</u>”ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ዛሬም <u>“እኔ ኃጢአተኛውን:-በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ ÷ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው÷ ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል፡ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ”</u> ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: (ት/ሕዝቅ 3÷18)

ዛሬም ስለ ኃጢአተኞች ነፍሱን አሳልፎ የሰጠውና እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣው÷በመጨረሻም በታላቅ ክብር ተመልሶ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ለእያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲህ ይላል፡ “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ:: እንግዲህ <u>ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ÷በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ÷ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ”</u> ይላል:: (ማቴ 28÷18-20) ከዚህ ነፃ ሊሆን የሚችል ክርቲያን የለም:: ጌታ እግዚአብሔር ለሚጠፉት ነፍሳት ፍቅርና ሸክም ይስጠን:: አሜን:: … … ይቀጥላል::

ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶአል::



ወደ ሰማይ አርጎአል በክብር ይመለሳል::

# “እረፉ÷እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፡”

(መዝ 46÷10

ብዙዎቻችን ይህንን ጥቅስ እናውቃለን፡ ነገር ግን የጥቅሱን ዕውነተኛ ይዘት ብናስተውል÷ በነገር ሁሉ በጌታ ማረፍ እንችላለን:: ምክንያቱም እርሱን ተማምነን በምናርፍበት ጊዜ እግዚአብሔር በችግሮቻችን ላይ በመገለጥ አምላክነቱን ያሳያል::ማረፍ ማለትም እንዲሁ መቀመጥ(መቦዘን) ሳይሆን÷የአካልን የአዕምሮንና የስሜትን እንቅስቃሴ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል በመግዛት÷ በዕምነትና በርጋታ መጠባበቅ ነው::

ጌታ ሆይ በዚህ ጉዳይ ድረስልኝ ካሉት በኋላ የማይሰማ ወይም የሚጨክን ይመስል÷ መጨነቅና መታወክ ትርፉ ጉዳት ብቻ ነው:: እንዲህ የሚሆኑ ሰዎች የለመኑትን ሁሉ በራሳቸው ጊዜ መቀበል እንዳለባቸው የሚያስቡ ሰዎች ናቸው:: ለማረፍ ግን እግዚአብሔር በወደደው መንገድ ሕይወቴን ይምራ ማለት ያስፈልጋል:: ጌታ በመልካም አባትነቱ÷ከመልካም ሁሉ ሳያጒድል÷ እየጠበቀ የሚመራ አባት መሆኑን ማመን ያስፈልጋል:: እንዲህም ከሆነ:-“ነፍሴ ሆይ በአምላክሽ ተማምነሽ እረፊ” ለማለት ይቻላል::

በሕይወትህ ውስጥ የሚያስቸግርህ ነገር ካለ በፀሎት በፊቱ ካስታወቅህ በኋላ ዕረፍ÷እግዚአብሔርም አምላክ መሆኑን ታያለህ:: የሚያሳስብህ ነገር መኖሪያ ፈቃድ÷ የቤተሰብ ችግር ወይም የጤና ችግር ቢሆን:- “እረፉ÷ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ” ይላል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር፡ በዚህስ ጌታ ካልደረሰልኝ አይሆንም ባልክባቸው ነገሮች ሁሉ:- “ዕረፉ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ” ይላል ጌታ እግዚአብሔር::በዕረፍትና በጸጥታ ውስጥ ብቅ ይልልሃል:: እርሱ የሰላምና የዕረፍት አምላክ ስለ ሆነ÷ በጸጥታ ሥፍራ መገኘት ባሕሪው ነውና:: “እረፉ÷ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፡” ያለው ለዚህ ነው:: እግዚአብሔር ይመስገን::

❖❖❖❖❖❖❖

## ፍጥረት (ከቀደሙት ደብዳቤዎቻችን የተደገመ)

ከፍ ብለው በሕዋው ላይ የከዋክብት ድምቀታቸው
ሰማይ ለሰማይ ሲንሳፈፍ በነፋስ ግፊት ደመናው
የሰማይም ጠል ነጠብጣብ ወርዶ ምድሪቱን ማርካት
የረካችውም ምድር አምራ ስትላበስ በዕጽዋት፤
በሚበላ÷በሚለበስ ወይ እንደ ጌጥ ወይ መድኃኒት
እንዲህ ምጥን÷እንዲህም ውብ÷እንዲህ ግሩም የአምላክ ፍጥረት::

እንዴት ግሩም እንዴትስ ድንቅ÷ልብ ብለን ስናጤነው
የዓለም ሁሉ እንስሳት በዱር ውለው በዱር አድረው
ቢሳሳቱ መካሪ÷ ወቃሽ ከሳሽ ሳይኖራቸው
የማይሠሩ የማይጥሩ ሁሌ ምግብ ሳያጥራቸው
ማሳደግያው ሳይገዳቸው ያለስጋት ሲዋለዱ
ባልና ሚስት ተጣልተው ልጆች ጥለው የማይሄዱ
ወልደው በዝተው እንደ ሕጉ እያረጁ የሚያልፉ
የእንስሳት ፍጥረታቸው እንዴት ይሆን ፅንሱ ዘርፉ

አንዱ ዓሣ ከውኃ አዳር÷ ሌላም አውሬ ዱር የሚኖር
ይኸ በምድር ተንቀሳቃሽ ያኛው በአክናፍ የሚበር
እግረኛው ልጁን ሲያጠባ ከናፌው ባፉ የሚያበላ
እንደ ርግብ እንደ ንስር እንደ አናብስት እንደ ዋላ
የምድር ግርማ የዓለም ውበት ሁሉ ዓይነት እንስሳት
የአምላካችን ምስክሮች የጌታ እግዚአብሔር ፍጥረታት::

መላኩ ትዕዛዙ

ኢየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::